በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 5


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

- ተጋቢዎች ‹‹ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆናችሁበት››፣ ምስጢረ ጋብቻ (ተክሊል) ከተፈጸመ በኋላ፣ ሁለታችሁ ‹‹በክርስቶስ አንድ እንደሆናችሁ›› ካመናችሁ በግኑኝነታችሁ መካከል ግልጽነትና መተማመን ይነግሳል። በዚህም የተነሳ ከትዳር አጋራችሁ የምትሰውሩት ምንም ነገር አይኖርም ፈጽሞ ለመዋሸትም አትሞክሩም።
- እግዚአብሔር ለተጋቢዎች የነበረው የመጀመሪያው እቅድ ለእግዚአብሔርና እርስ በራሳቸውም ግልጽ እንዲሆኑ ነበር። ነገር ግን ሲበድሉ መዋሸት፣ ስሕተታቸውንና ውሸታቸውን በሐሰት መደበቅ ጀመሩ፤ በዚህም የተነሳ የግልጽነትንና የታማኝነትን በረከትና ስጦታ አጡ።
- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዚህ ዓለም የመጣው የሰውን የቀደመ ጸጋውን ሊመልስለት ስለሆነ እንደ ‹‹ሕጻናት›› በእምነት፣ ፍቅርና ግልጽነት በቀላሉ በዚህ ዓለም እንድንኖር ጠይቆናል።
- ‹‹እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና።›› *ቆላ 3:9።*
- በዘመናችን በሰዎች ግኑኝነት ይልቁንም በባለትዳሮች መካከል መተማመን፣ ጽንዓት፣ ግልጽነት አለመኖሩን መመልከት እጅግ አስገራሚ ነው።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

- ሚስቶች በባሎቻቸው ሥነ ምግባር፣ ጓደኞቻቸውን፣ ግኑኝነታቸውን፣ ችሎታቸውን (ጥበባቸውን) በተመለከተ እምነት እንደሌላቸው በምሬት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁ ባሎችም በሚስቶቻቸው ላይ እምነት እንደማያሳድሩ፣ ከጋብቻቸው በፊት ከሌሎች ጋር የነበራቸውን ግኑኝነት፣ ለውሳኔ ችኩሎች ናቸው፣ በሌሎች ሰዎች አመለካከት ይወሰዳሉ ወይም ይሸነፋሉ ብለው በማመን ቅሬታቸውን ያሰማሉ፡፡
- ከሁሉ አስቀድሞ ግልጽነትና ታማኝነት የጋብቻ ቃል ኪዳን ካደረግንበት ጊዜ አንስቶ መኖር እንዳለበት እንተማመን፡፡ ከትዳር አጋራችን ጋር ከተዋወቅንበት ቀን አንስቶ ግልጽና ታማኝ እንሁን፡፡
- **ለውሳኔ ያመቻችሁ ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፡-**
  - የትዳር አጋራችን በተደጋጋሚ ሲዋሽን/ስትዋሽን ገጥሞን ያውቃል?
  - በማንኛውም ጉዳይ ሲነጋገር/ስትነጋገር ነገሮችን ያጋንናል/ታጋንናለች?
  - ከመጋባታችሁ በፊት በነበረው/ራት ግኑኝነት ዙሪያ ስከ መጥፎ ሥራዎች የሚያነገግሩ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ይጮሃል/ትጮሃለች?

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

- **ለውሳኔ ያመቻችሁ ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፡-**
  - ቃልኪዳን ከማድረጋችሁ በፊት ተፈጽሞ ሆን ብሎ ሳይነገረን የተደበቀ ነገር ገጥሞን ያውቃል?
  - ይህ ጉዳይ ስለምን እንደተደበቀን ተነጋግረን ተመሳሳይ አጋጣሚዎች ቢፈጠሩ ደግሞ ተመሳሳይ ጥፋት እንደማይፈጸም ተነጋግረን እናውቃለን?
  - የትዳር አጋራችን ግኑኝነታችንን ወይም የወደፊት ሕይወታችንን ሊጎዳ በሚችል መልኩ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንደማያወያዩን አረጋግጠን እናውቃለን?
  - ውሸት ከሁኔታዎችና ከጓደኞች ለማምለጥ ሲባል የትዳር አጋራችን የዘወትር ልምድ ሆኖ አጋጥሞን ያውቃል?
  - ስለዚህስ መጥፎ ልምድ ተነጋግረን ነገር ግን ሊቀይረው/ልትቀይረው የማይፈልገው/ትፈልገው አመል መሆኑን አረጋግጠን እናውቃለን?
- **ታዲያ እንደዚህ ከሆነ ቀድሞውኑ መተማመን ወደሌለበት እንዲህ ያለ ሕይወት ራሳችንን አመቻችተን ስለምን ገባንበት?**

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

- የተወደዳችሁ ወንዶችና ልጃገረዶች! ለማመን የምትቸገሩበትን/ባትን፣ አብሮ መታየት የማይፈልገውን/የማትፈልገውን፣ ጭንቀቱ/ትዋ ለትክክለኛ ማንነት ሳይሆን በውጪ ለሚታየው ነገር ብቻ የሆነውን/ችውን፣ መዋሸት የሚቀለውን/ላትን፣ መላ ሕይወቱ/ቷ በድብቅነት የተሞላ፣ ግራ የሚያጋቡ ተግባራትን የሚፈጽመውን/ምትፈጽመውን የትዳር አጋር አድርጋችሁ ለመኖር አትወስኑ፡፡
- ሐሰተኝነት ‹‹ጸጋችን ተገፎ - ወድቀን የነበርንበት›› አንድ የውድቀት ሕይወት ገጽታ ነው፤ ይህም በተጠመቅንበት ጊዜ ተቀብሮ ንስሐ በገባንና ኃጢአታችንን በተናዘዝን ቁጥር እየተቀበረ የሚቀጥል ነው፡፡
- ግልጽነትና ታማኝነት ደግሞ ከድኅነት በኋላ የ‹‹ታደሰው›› የሰው ተፈጥሮ ገጽታ ሲሆን ተጋቢዎቹ በምስጢረ ተክሊል በክርስቶስ አንድ ሆነው ሲታተሙ ለሚጀምሩት አዲስ ሕይወት ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡
- ግልጽነትና ታማኝነት ስኬታማ ለሆነ ክርስቲያናዊ ትዳር መሠራታዊ ምሰሶዎች ናቸው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

**የተወደዳችሁ ባሎችና ሚስቶች!**

- ለራሳችሁ፣ ለትዳር አጋራችሁ፣ እንዲሁም ከሁሉም በላይ ውስጣችንን ለሚመለከትና ለሚመረምር ብሎም ፈጽመን ልናታልለው ወይም ልንዋሸው ለማንችለው ለእግዚአብሔር ታማኞች እንሁን፡፡ ‹‹እናንተ ደንቆሮዎች፥ የውጭውን የፈጠረ የውስጡን ደግሞ አልፈጠረምን?›› *ሉቃ 11፡40፡፡*
- ከትዳር አጋራችሁ ምንም ነገር አትደብቁ፤ ቅናትና ጥርጥርም ግኑኝነታችሁን እንዲያጠፉ አትፍቀዱ፡፡
- በራሳችሁና በትዳር አጋራችሁ ፍጹም መተማመንን እንድታሳድሩ ሊያደርጋችሁ በሚችለው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጣበቁ፡፡
- ኃቲአታችሁን ተናዛችሁ ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም እንደተረሳችላችሁና እንደተተወችላችሁ እመኑ፡፡
- ግልጽነት የመተማመን ምንጭ ሰሆን፣ መተማመንም የአንድነትና የመተሳሰር ምንጭ፣ አንድነትና መተሳሰርም የመቀጠልና ተረጋግቶ የመቀመጥ ምንጭ ናቸው፡፡ ‹‹ምንጭህ ቡሩክ ይሁን ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ፡፡›› *ምሳ 5፡18፡፡*

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

**የተወደዳችሁ ባሎችና ሚስቶች!**

- በተጨማሪም የትዳር አጋራችንን መጠራጠርና አለማመንን ማስወገዳችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
- አለመተማመን በርካታ ተጋቢዎችን ወዳልተፈለገ ደረጃ የሚያዳርስ፣ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትልባቸው አደገኛ ነገር ነው፡፡ ‹‹ፍቅር ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል፡፡›› ***ቀዳ ቆሮ 13፡7፡፡***

***አለመተማመን የሚያስከትሉ ጥቂት ምክንያቶችን እንደሚከተለው እንመልከት፡-***

1. **የግኑኙነት መስመሮች መቋረጥ**

- በተጋቢዎች መካከል ቀጣይነት ያለው ግኑኙነት ከሌለ በቀላሉ መግባባት ያቅታቸዋል፣ የተነገረውን ነገር አጣሞ መተርጎም ይፈጠራል ይህም አለመተማመንን ያስከትላል፡፡
- ተከታታይነት ያለው ግኑኙነት ወይም መነጋገር ካለ ግን በነገሮች ያለመግባባት እድሎች በከፍተኛ መጠን ይቀንሳሉ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

**ግልጽነትና ታማኝነት**

***አለመተማመን የሚያስከትሉ ጥቂት ምክንያቶችን እንደሚከተለው እንመልከት፡-***

2. **በራስ መተማመን ያለመኖር**

- በራሳችን መተማመን ከጎደለን የትዳር አጋራችንንም ለማመን የሚኖረን ዕድል በከፍተኛ ደረጃ ያነሰ ይሆናል፡፡
- በራሱ መተማመን ያለው ሰው ሌሎች ሰዎች የሚናገሩትን ወይም የሚሠሩትን ሁሉ ማመን ይከብደዋል፡፡ እንዲያውም ሌሎች እየቀለዱበት/ባት ያሉ ሊመስለው/ላት ይችላል፡፡

3. **ይቅር ለማለት አለመቻል**

- የትዳር አጋራችንን ይቅር ማለት ካልቻልን ፈጽማችሁ መተማመን አንችልም፤ በዚህም የተነሳ ዘወትር በተጠራጣሪነት ተገኝተን ስለሕይወታችን መልካም ራዕይ የሌለን እንሆናለን፡፡
- በባለትዳሮች መካከል የሚኖር የይቅር ባይነት ሕይወት ባለትዳሮቹን የጸሎትና፣ ዘወትርም ይቅር በማለትና በመርሳት የትግል ሕይወት ውስጥ እንዲኖሩ ይረዳቸዋል፡፡
- ይህን ታላቅ ስጦታና በረከት እንዴት እንደምንቀበል ለማወቅ ያስችለን ዘንድ ዘወትር ወደንስሐ አባታችንም በመገስገስ ምክራቸውን መቀበል ያስፈልገናል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

*አለመተማመን የሚያስከትሉ ጥቂት ምክንያቶችን እንደሚከተለው እንመልከት፡-*

3. ይቅር ለማለት አለመቻል

- ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዳችን በተመሳሳይ ችግር ወድቀን ስንገኝ ይቅር ተብለን መታለፋችን አስፈላጊያችን እንደሆነ አንዘንጋ፡፡
- እንዲሁም ኃጢአታችን ምንም ያህል የበዛ ቢሆን ጌታችን ኃጢአታችንን እንዴት እንደሚረሳልንና ይቅር እንደሚለን እናስተውል፡፡
- የተወደዳችሁ ባልችና ሚስቶች! እርስ በርስ ይቅር መባባልን ተማሩ! ጌታችን ‹‹የሰውነትህ መብራት ዓይንህ ናት፡፡ ዓይንህ ጤናማ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ብሩህ ይሆናል፡፡ ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ግን ሰውነትህ ደግሞ የጨለመ ይሆናል፡፡›› *ሉቃ11፡34፡፡* እንደተናገረው ነገሮችን መልካም አድርጎ የሚመለከት ዓይን፣ የተባረከና መልካም የሆነ ነገርን የምናስብ መሆን እንችል ዘንድ እንጣጣር!
- ጆሮአችን በትዳር አጋራችን ላይ ያለን እምነት የሚሸረሸርበት ‹‹ክፉ ነገር›› ይሰማ ዘንድ አንፍቀድለት፡፡ ይህም ይሆንልን ዘንድ ‹‹ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ››፣…

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 5

## ግልጽነትና ታማኝነት

- ‹‹ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምሕረትህ ትደረግልኝ››፣ ‹‹ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በነገር ሁሉ ርዳኝ፤››… እያልን ከመዝሙረ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቃል በመውሰድ ፈጽመን በሚያፋቅረን ኃይለ ቃል እንነጋገር፡፡
- በአጭሩ ክፉ ነገር ሕይወታችንን በክፉ ሐሳብ ይገዛ ዘንድ አንፍቀድለት፡፡ ‹‹ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት፡፡›› *ኤፌ 4፡27፡፡*
- አለመተማመን ሲገጥመን የትዳር አጋራችን ስለጉዳዩ እንዲያስረዳ/ታስረዳ ዕድል እንስጥ፡፡ ካልተሳሳተ/ች ግን ባለማመናችን የተነሳ ለፈጠርነው ስሕተት ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል፡፡
- በዚህ ዓይነት መንገድ ስሕተት የፈጠሩትንም ይቅር ለማለትና ለመርሳትም እንዘጋጅ፡፡
- ‹‹ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው፡፡›› *ማቴ 19፡6፡፡* እንደተባልን እንርሳ፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org